# የሥራ ፈቃድና አቤቱታዎች

በሥራ ጥራት ላይ ልዩነት እንደሚኖር ይገምቱ። ስቴቱ መሠረታዊ የሆነ የአገልግሎት ደረጃ አንዳለ ያረጋግጣል፡ ነገር ግን የሥራ ፈቃድ ያላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች ሰፋ ያለ የተለያየ ዓይነት ጥራት ያለው አገልግሎት ያቀርባሉ። ልጅዎ ለሚያስፈልገው ዋና ወሳኙ እርስዎ ነዎት።

**የሥራ ፈቃድ ስላለው የመዋለ ሕጻናት ፕሮግራም መረጃ ማግኘት እንዴት እችላለሁ?**

ልጅዎን የሥራ ፈቃድ ወዳለው መዋለ ሕጻናት ለማስመዝገብ ካሰቡ ለተገቢው ፈቃድ ሰጪ ክፍል በመደወል ፕሮግራሙ አቤቱታ ቀርቦበት እንደሆነ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ ክፍል በመደወል ማወቅ ይችላሉ። በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ለሚገኝ ባለሥራ ፈቃድ መዋለ ሕጻናት ፕሮግራም (የቤተሰብ መዋለ ሕጻናት ቤት ወይም ማዕከል) የሥራ ፈቃድ ሰጪ ክፍል ስም ለማግኘት እባክዎን 1-866-482-4325 ይደውሉ። ደግሞም ይህን መረጃ በኦንላየን በሕብረተሰብና ጤና አገልግሎት ጽ/ቤት በኩል ማግኘት ይችላሉ።

የልጅ ማሳደጊያና የቅድመ ትምህርት ክፍል — ሲያትል **ማሳሰቢያ፡ የ 4A ዌብ ሳይት በአሁኑ ሰዓት ሥራ ላይ አልዋለም — ለመረጃ እባክዎን 206 721-6941 ይደውሉ።**

የልጅ ማሳደጊያና የቅድመ ትምህርት ክፍል — ኬንት

ደግሞም ስለ አንድ ፕሮግራም የሥራ ፈቃድና አቤቱታ ጉዳይ የስቴቱን ሥራ ፈቃድ ያላቸው መዋለ ሕጻናት መረጃ ማግኛን ዌብ ሳይት ላይ በመመልከት ወይም 1-866-48CHECK በመደወል ሊያጣሩ ይችላሉ።

**የሥራ ፈቃድና አቤቱታዎች**

የልጅ ማሳደጊያና የቀደም ትምህርት ክፍል በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ የሚገኝ የሕብረተሰብና ጤና አገልግሎት ጽ/ቤት (ዲኤስኤችኤስ) ክፍል ነው። ዲኤስኤችኤስ ለመዋለ ሕጻናት ማዕከላትንና ለቤተሰብ መዋለ ሕጻናት ቤቶች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል እንዲሁም ቁጥጥር ያደርጋል፡ ፈቃድ ባላቸው የአገልግሎት ድርጅቶች ላይ የሚቀርቡትን አቤቱታዎች ይመረምራል፡ እንዲሁም ፈቃድ ስላላቸው የአገልግሎት ድርጅቶች መረጃዎችን ያቀርባል።

በዝምድና ለማይገናኙት ልጅ መደበኛ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ከዲእስኤችኤስ ፈቃድ ማግኘት አለበት። ፈቃዱ ፕሮግራሙ በዋሽንግተን ስቴት የተወሰነውን ትንሹን ነጥብ እንደሚያሟላ ያመለክታል።

**አቤቱታ የማቀርበው እንዴት ነው?**

የሥራ ፈቃድ ሁኔታን አለማክበር ወይም በመዋለ ሕጻናት ወይም በቤተሰብ የመዋለ ሕጻናት ቤት ልጅን ስለማንገላቀል ጉዳይ ለማመልከት፡ (206) 721-6500 ደውለው ከሚቀርበው አማራጭ ቁጥር "5" ይምረጡ። አቤቱታ ስለማቅረቡ ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎን ይደውሉልን።

- ስልክ፡ (206) 329-1011
- ኢ-ሜይል፡ parserve@childcare.org

**በ'አሜሪካንኖች ዲሳቢሊቲስ አክት' መሠረት ያለኝ መብት ምንድን ነው?**

'የአሜሪካኖች ዲሳቢሊቲስ አክት' በ 1992 ውስጥ የወጣ የፌደራሉ የሕዝብ መብቶች ሕግ ነው። ሕጉ በአካል የተጎዱ ሰዎች በሥራ ቅጠር፡ በስቴትና በአካባቢ ሕዝባዊ አገልግሎቶችና፡ ቅድመ ትምህርት ቤቶች፡ የመዋለ ሕጻናት ማዕከላትና የቤተሰብ መዋለ ሕጻናት ቤቶች በመሳሰሉ የሕዝብ መገልገያዎች በእኩልነት አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው ይገልጻል። ኤዲኤ (የአሜሪካኖች ዲሳቢሊተሷ አክት) የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢዎች ያካል ጉዳት ባለበት ሰው ላይ ባካል በመጎዳቱ ምክንያት አድሎ እንዳያደርጉ ይጠይቃል። የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢዎች በፖሊሲያቸውና በአሠራራቸው ላይ ለውጦችን ማድረጉ ፕሮግራማቸውን ባጠቃላይ የሚቀይር ካልሆነ በስተቀር ልጆችን ለማስተናተገድ ሁነኛ ማሻሻል ማድረግ አለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ ወይም አቤቱታን ለማቅረብ እባክዎን ለጀስትስ ዲፓርትመንት ይደውሉ።

- ስልክ፡ 1-800-514-0301
- ዌብ ሳይት፡ http://www.usdoj.gov/crt/ada/adahom1.htm

**በተጨማሪም ይመልከቱ**

- የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ምንርጫዎቹ ምንድን ናቸው?
- የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቅራቢን ስለመምረጥ